**የመሰብሰቢያ ክፍል እና የማጥኛ ክፍል አጠቃቀም መመሪያ**
**መስከረም 9 ቀን 2013 የተሻሻለ**

ይህ መመሪያ በሁሉም የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ቤተ መፃህፍት (DCPL) ህንፃዎች የመሰብሰቢያ ክፍሎችን እና የማጥኛ ክፍሎችን አጠቃቀም ያስረዳል። የቤተ መፃህፍት የመሰብሰቢያ ክፍሎች እና የማጥኛ ክፍሎች ቤተ መፃህፍቱ ራዕዩን እንዲያሳካ በዋናነት እንዲጠቀምባቸው የተዘጋጁ ናቸው። ቤተ መፃህፍቱ አገልግሎቶቹን ለተጠቃሚዎች ለመስጠት በጾታ፣ ዘር፣ ፍልስፍና፣ እምነት፣ ቀለም፣ ባህል ወይም ብሔር፣ አገር፣ ዕድሜ፣ የጾታ ዝንባሌ፣ የግለሰብ የአኗኗር ዘይቤ፣ የፖለቲካ አመለካከት ወይም በአካል ጉዳት አድሎ አያደርግም። የመሰብሰቢያ ወይም የማጥኛ ክፍልን ለመጠቀም አያስከፍልም።

የመሰብሰቢያ ክፍል ወይም የማጥኛ ክፍል ከቤተ መፃህፍት ጋር ለተገናኘ ሥራ እስካልተያዘ ድረስ በከተማ የተቀነባበረ እንቅስቃሴ ወይም በቤተ መፃህፍት አጋር ለተሰናዳ ዝግጅት እንዲሁም የዲ.ሲ የህዝብ ቤተ መፃህፍት ካርድ ያለው የህበረተሰቡ አካላት የቤተ መፃህፍቱ ድህረ ገጽ ላይ በተጠቀሰው የቤተ መፃህፍት ደንቦችና ህጎች መሠረት ክፍሉን ለመጠቀም ሊያመለክት ይችላል። እያንዳንዱ ጥያቄ በቀረቡት የጥያቄዎች ብዛት በተናጠል ይታያል። የክፍሎች መኖር፣ የቤተ መፃህፍቱ ቅድሚያዎች እና የማስያዣ ጥያቄዎች በቤተ መፃህፍቱ ሊለወጡ ወይም ሊሰረዙ ይችላሉ።

የመሰብሰቢያ ክፍል መያዣዎች በቅድሚያ የመጣ በቅድሚያ ይስተናገዳል በሚለው ሁለት (2) ወር ቀደም ብለው ይታያሉ። የቤተ መፃህፍቱን ህንፃዎች ፍትሃዊ አጠቃቀም ለማረጋገጥ ቤተ መፃህፍቱ በቡድን ለሶስት (3) ተከታታይ ሰዓት እና በመላው ቤተ መፃህፍት በወር ከሶስት (3) ስብሰባዎች እንዳይበልጥ የመገደብ መብቱ የተጠበቀ ነው። ማስታዎስ የሚገባው የተለያዩ ስሞችን በመጠቀም ተመሳሳይ ቡድንን በመመዝገብም ሆነ ቡድኑ የተለያዩ ስሞችን ተጠቅሞ በመመዝገብ ይህ ገደብ ሊቀር እንደማይችል ነው። የማጥኛ ክፍሎችን መጠቀም የሚቻለው በቀን ሁለት ጊዜ ብቻ ነው።

የቤተ መፃህፍት የመሰብሰቢያ ክፍሎችን ወይም የማጥኛ ክፍሎችን ለመጠቀም ፈቃድ ማግኘት በምንም መልኩ ቢሆን የኮሎምቢያ ዲስትሪክ የህዝብ ቤተ መፃህፍትን ድጋፍ እንደማግኘት አይቆጠርም። ይህንኑ ድጋፍ በማስመልከት ምንም ዓይነት የህትመትም ሆነ የኤሌክትሮኒክ ማስታወቂያ እንዲሁም የቤተ መፃህፍቱን ሎጎ (ምልክት) መጠቀም አይፈቀድም።